# በርቀት ለሚካሄዱ ችሎቶች (ሪሞት ሂሪንግስ) ለመከታተል የሚያገለግሉ ጠቃሚ ምክሮች- የወንጀለኛ ክፍል (ክሪሚናል ዲቪዥን)

*በኮቪድ-19 ወይም ኮሮናቫይረስ ወረርሽኝ ምክኒያት በርካታ ፍርድ ቤቶች ዝግ ናቸው። የፍርድ ቤት ችሎትዎ በርቀት ሊካሄድ ይችላል። ይህ ማለት ችሎቱን የሚከታተሉት ወደ ፍርድ ቤት በአካል በመምጣት ሳይሆን በቴሌፎን ወይም በቪድዮ ኮንፈረንስ ይሆናል ማለት ነው። እንዴት መዘጋጀት እንዳለብዎ አንዳንድ ጠቃሚ ምክሮች እንደሚከተለው ይቀርባሉ።*

**በርቀት የሚካሄድ ችሎት እንዳለኝ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?**

ችሎትዎ በርቀት የሚካሄድ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ወይም ጠበቃዎ ይነግርዎታል። ኢ-መይል በመላክ፣ ደብዳቤ በፖስታ በመላክ ወይም በመደወል ሊነግርዎት ይችላሉ።

**በርቀት በሚካሄደው ችሎት እንዴት መሳተፍ እችላለሁ?**

በርቀት በሚካሄድ ችሎት እንዴት መሳተፍ እንደሚችሉ ደረጃ-በደረጃ የሚያሳዩ መመርያዎች ፍርድ ቤቱ ወይም ጠበቃዎ ይሰጥዎታል።

በጽሁፍ የተላከልዎ ማስታወቂያ የጠፋብዎ ከሆነ መመርያዎቹ ይሰጥዎት ዘንድ የወንጀለኛ ክፍልን (ክሪሚናል ዲቪዥን) በሚከተለው ይደውሉ፡

(202) 879-1373

**ችሎቱ ከሚካሄድበት ቀን አስቀድሜ ማድረግ የሚገባኝ ነገር አለ?**

ቴሌፎን ወይም ኮምፒውተር ስለሌልዎት በችሎቱ መሳተፍ የማይችሉ ከሆነ ወዲያውኑ ፍርድ ቤቱንና ጠበቃዎን ያሳውቁ።

ማስረጃ፣ ምስክሮች ወይም ሌሎች ሰነዶች ማስረከብ የተመለከቱ ጉዳዮች ጨምሮ የህግ እርዳታ ለማግኘት ጠበቃዎን ማግኘት ሊያስፈልግዎ ይችላል።

ማመቻቸትና የቋንቋ ተደራሽነት (አኮሞዴሽንስ ኤንድ ላንጉጅ አክሰስ)፡ ለችሎትዎ አስተርጓሚ ወይም ሌላ ማመቻቸት የሚፈልጉ ከሆነ ፍርድ ቤቱንና ጠበቃዎን ያሳውቁ።

**ለችሎቱ የሚያገለግሉ ጠቃሚ ምክሮች**

- ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብለው ችሎቱን ይቀላቀሉ!
- ኮምፒውተርዎን ወይም ቴሌፎንዎን ይሙሉ (ቻርጅ ያድርጉ)፣ ችሎቱን ለመቀላቀል በቂ ደቂቃዎች እንዳለዎትም እርግጠኛ ይሁኑ። የብቻ (ፕራይቬት) እና ጸጥ ያለ ቦታ ይፈልጉ። የሚቻል ከሆነ ችሎቱ በሚካሄድበት ወቅት ክፍል ውስጥ ብቻዎት ይሁኑ። በሚቻለው መጠን ትኩረትዎ ከሚረብሹ ነገሮች ይቆጠቡ። ክፍሉ ውስጥ ሌሎች ሰዎች ከርስዎ ጋር ካሉ ችሎቱ በሚካሄድበት ወቅት ጸጥ እንዲሉ ይጠይቋቸው።
- እየተናገሩ ካልሆነ ማይክሮፎንዎን ድምጸ-ከል (ሚዩት) ያድርጉ።
- በቴሌፎንዎ ወይም ኮምፒውተርዎ ያሉትን ሁሉም ድምጾች ድምጸ-ከል (ሚዩት) ያድርጉ።
- መዝገቡ ግልጽ ይሆን ዘንድ መናገር ከመጀመርዎ በፊት ስምዎን ይናገሩ። በችሎቱ ያለዎትን ተራ ለይቶ ለማሳወቅ ዝግጁ ይሁኑ (ለምሳሌ፡ ታዛቢ፣ ከሳሽ፣ ተከላካይ፣ ምስክር፣ ወዘተ)።
- እየተናገሩት ያሉትን ተሳታፊዎች በሙሉ ይሰሙት ዘንድ በዝግታና ግልጽነት ባለው አኳሀን ይናገሩ።
- መዘግየት (ላግ) ካጋጠመ ከመናገርዎ በፊት ለአፍታ ያቁሙ (ፖዝ ያድርጉ)። ከቻሉ የጆሮ ማዳመጫ (ሄድሰት ወይም ሄድፎንስ) ይጠቀሙ። እንዲህ ቢያደርጉ እጆችዎንና ድምጽዎን በበለጠ ነጻ እንዲሆኑ ያስችላል።
- ሌላ ሰው እየተናገረ እያለ ላለመናገር ይሞክሩ። በአንድ ጊዜ መናገር የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነው። ሌላ ሰው እየተናገረ እያለ ቢናገሩ ዳኛው ሊያዳምጥዎ አይችልም።
- ለችሎቱ የሚጠቀሙባቸው ሁሉንም ሰነዶችዎ ከፊትዎ ያድርጉ።
- ማስታወሻዎች ይወስዱ ዘንድ እስክርቢቶና ወረቀት ይኑርዎት።

**በቪድዮ ለሚካሄዱ ችሎቶች የሚያገልግሉ ልዩ ጠቃሚ ምክሮች**

**(ለተጨማሪ መረጃ እዚህ ይጫኑ)**

- ቀደም ብለው የፍርድ ቤቱ የችሎት ሶፍትዌር የሆነውን ዌብኤክስን (WebEx) በማውረድ (ዳውንሎድ በማድረግ) ይሞክሩት! ፍርድ ቤቱ ችሎቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ የዌብኤክስ ሊንክ ይሰጥዎታል።
- ካሜራው በአይንዎ ልክ (አይ ለቨል) ያስተካክሉት። ቴሌፎንዎን እየተጠቀሙ ከሆነ ቴሌፎኑን ሳይይዙ ይመለከቱት ዘንድ አስደግፈው ያስቀምጡት።
- ሲናገሩ ወደ ካሜራው ይመልከቱ፣ በቪዲዮው ከመንቀሳቀስም ይቆጠቡ።
- ወደ ፍርድ ቤት ሲመጡ የሚለብሱት አይነት ልብስ ይልበሱ።
- ከኋላዎ ብሩህ መብራቶች በሌለው በደንብ ብርሃን ባለው ክፍል ውስጥ ይቀመጡ።
- የሚቻል ከሆነ ከፊት ለፊቱ የሚቀመጡበት ባዶ ግድግዳ ይፈልጉ። ዳኛው ሁሉንም በስክሪንዎ የሚኖረው ስለሚመለከቱ ትኩረት የማይረብሽ ቦታ ይምረጡ።